ሰ ር/መ/ቁጥር--132492

ፍትህ 22/2009 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አለ. መሀመድ

ተፈሪ ገብሩ

ቀነን ቂጣታ

አይሻሽም መለሰ

ፀሀይ መንክር

አመልካች ------- አቶ ማማይ አበራ

ተጠሪ----------የትግራይ ክልል ፍትህ ቢሮ ዐ/ህግ ክብረ አብ ገ/እግዚ ብሔር

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው፣አመልካች በ15/10/2008ዓ.ም.በተጻፈ፣የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት እንዲታረምለት አቤቱታ በማቅረቡ ነው ፡፡በሰር ፍርድ ቤት፣ዐ/ህግ በተከሳሹ ላይ የአቀረበው ክስ፡-ተከሳሹ የወንጀል ህግ ቁጥር 680(3)ለ በመተላለፍ የ3 ግለሰቦች ንብረት የሆኑ ከብቶች፣1ኛ/የአቶ ማሙ ንጉሴ 8 ከብቶች ግምታቸው 63,000 ብር፣2ኛ/ የአቶ ማሙ ገ/ስላሴ ከብቶች ግምታቸው 48,500 ብር፣3ኛ/የአ፡ አብረሃ መብራቱ 3 ከብቶች ግምታቸው 26,000 ብር ፣4ኛ/የአቶ ሀጎስ አሰፋ 1 ከብት ግምቷ 10,000 ብር፣5ኛ/ የቄስ አፈወርቅ ረዳ 2 ከብቶች ግምታቸው 20,000 ብር፣6ኛ/የአቶ ደሴ ገ/ሀይወት 2 ከብቶች ግምታቸው 20,000 ብር 7ኛ/ የአቶ ገ/ዋህድ ዋልታይ 1 ከብት ግምቷ 10,000 ፣8ኛየአቶ አግደው ገ/መድህን 1 ከብት ግምቱ 9,000 የ8 ሰዎች ከብቶች ብዛታቸው 25(ሃያ አምስት) በድምር 206,500 (ሁለት መቶ ሰድሳት ሺ አምስት መቶ ብር ብቻ) የሆነ ንብረት ተከሳሽ በ02/08/2007 ዓ.ም ከምሽቱ 1፡00 ሰዓት ሲሆን ከሌሎች ሁለት ሰዎች ጋር ሽመሃን በፈጸመው የከባድ ስርቆት ወንጀል ተከሷል ብሎ በሰር ዐ/ህ መራ ወረዳ ፍርድ ቤት

በተከሳሽ ላይ ዐ/ህግ የአቀረበው ሰምንት ክስ ቀርቦ ተከሳሽም ክሱን ከዶ የተከራከረ በመሆኑ ዐ/ህግ ምስክሮችን አቀርቦ በማሰማት ፍርድ ቤቱ ተከሳሽ እንዲከላከል ብይን የሰጠ ቢሆንም ተከሳሹ ያቀረባቸው 2 ምስክሮች ክሱን ሊያስተባብሉለት አልቻሉም በማለት ፍርድ ቤቱ በ8ቱ ክሶች ጥፋትኛ ነው ብሎ እያንደንዱን ክስ ቅጣት በመደመር 40 ዓመት ከ6 ወር የሚያስቀጣ ሆኖ በመገኘቱ ፍርድ ቤቱ በወ/ሀ/ቁጥር 108 መሰረት በተከሳሽ ላይ ከ25 ዓመት በላይ የእስራት ቅጣት ሊወሰን አይችልም በማለትና የግረቀኑን የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ በመቀበል በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 በእርከን 35 በተከሳሹ ላይ የ16 ዓመት ከ6 ወር ጽኑ እስራት ቅጣት ወስኗል።

አመልካች በዚሁ የሰር ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር ተሰኝቶ ይግባኝ ለትግራይ ምዕራባዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቀርቦ የተከራከረ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ የሰር ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔን በማጽናቱ አሁንም አመልካች በውሳኔ ስህተት ተፈጽመበታል በማለት ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቤቱታ አቀርቦ ሰበር ችሎቱ የቅጣት ውሳኔው ተደራራቢ ሆኖ የተወሰነበትን አግባብነት ለማጣራት ብሎ የሰበር አቤቱታውን የመረመረ ቢሆንም መልሶ የሰር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በማጽናቱ አመልካች አሁንም በሰር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህት ተፈጽሞበታል በማለት የአቀረበው የሰበር አቤቱታ ነው።

ይህ የሰበር ችሎቱም በአመልካች ላይ የተወሰነበትን የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔ ከወንጀል ሀጉ አንቀጽ 60(ሐ)እና61 አንጻር አግባብነትን ለመመርመር ሲባል አቤቱታውን ለሰበር ችሎት አስቀርቦታል።ግራቀኙ በጽሁፍ ክርክራቸውን አቀርበው ተከራክረዋል። እኛም ጉዳዩን ያስቀርባል ከተባለበት ጭብጥ አንጻር፣ከወንጀል ሀጉ ግብና ዓላማ እንዲሁም አግባብነት ካላቸው የወንጀል ህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል።

በዚህም መሠረት አመልካች ሁመራ ማረሚያ ቤት በመሆን ለሰበር ችሎቱ በ15/10/2008 ዓ.ም.በተጻፈ የአቀረበው አቤቱታ ይዘት በአጭሩ፡-ወንጀሉ ተፈጸመ የተባለው በአንድ ቀን፣በአንድ ቦታ፣በአንድ ተቆጣጠሪ ስር ያሉትን ከብቶች በተመለከተ ነው።ምንም እንኳን ከብቶቱ የ8 ሰዎች ናቸው ቢባልም የዐ/ህግ ምስክሮች የመሰከሩት አንድ ሰው እንደሚጠብቃቸው ነው።ከብት ጠባቂው የሚጠብቃቸው ከብቶች የራሱ ወይም በውክልና የሚጠበቁ ስለመሆኑ አይታወቅም።በመሆኑም ተፈጸመ የተባለው ወንጀል አንድ ሰርቆት እንጂ 8 ሰርቆት አልተፈጸመም።የሰር ፍርድ ቤቶች ይህንን የአመልካች ክርክር አለግባብ የለፉብኝ በመሆኑ ሊታረም ይገባል።የሰርቆ ወንጀሉንም ከባድ ሰርቆት የሚያስብለው

ምክንያት የለም፣በመሆኑም በአመልካች ላይ ጥፋተኛነት ውሳኔ መወሰን የሚገባው ሰርቆት ወንጀል እንጂ በከባድ ሰርቆት ሊሆን አይገባል።

ክሱ የወ/ሀ/ቁጥር 669(3)ለን በመጥቀስ የቀረበው ዋናው ምክንት ዐ/ህግ ተከሳሽ የከባድ ሰርቆ ወንጀሉን የፈጸመው ከሌሎች ሁለት ሰዎች ጋር በመሆን መሆኑን አምኗል በሚል ነው።ነገር ግን ይህ ድምዳሜ ህግንና ማስረጃን መሠረት ያላደረገ ነው። ምስክሮች ፍርድ ቤት ቀርበው የመሰከሩት ምስክሮች ቃል ብቻ መሠረት አደርገው በመሆኑ ተቀባይነት የለውም።የዕምነት ቃል የሚሰጠው በተከሳሹ በነጻ ፍላጎት ሊሆን ይገባል።በመሆኑ የጥፋተኛነት ውሳኔ ሊወሰን የሚገባው በቀላል እስራት ሊሆን ይገባል ተብሎ ይታረም።ቅጣትን በተመለከተ ድርጊቱ በጨለማ የተፈጸመ ነው ተብሎ በከባድ ሰርቆት ክስ ከቀረበ በኋላ እንደገና ድርጊቱ በጨለማ ተፈጽሟል ተብሎ በድጋሚ የቅጣት ማክበጃ ሆኖ ቅጣት መክበዱ ህግን የተከተለ ባለመሆኑ ሊታረም ይገባል።የከብቶች ዋጋን በተመለከተም ዋጋቸው እንዲሁ ተጋኖ የቀረበ ነው እንጂ የተገመተ ባለመሆኑ ቅጣትን አለአግባብ አክብዷል።በመሆኑም ግምቱም ሊታረም የሚገባው በመሆኑ የሰር ፍርድ ቤቶች ከፍ ሲል የተጠቀሱትን ስህተቶች የፈጸሙ በመሆናቸው ፣ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ተብሎ ይታረም በማለት አመልካች ቅሬታውን አጠቃሏል።

ዐ/ህግ በበኩሉ በ2/04/2009 ዓ.ም በተጻፈ መልስ ሰጠ ሲሆን የክርክሩ ይዘት ባጭሩ፡- አመልካች የወ/ሀ/ቁጥር 669(3)ለ ተላልፎ የ8 ግለሰቦች 25 ከብቶችን በሌሊት መስረቁ በሰር ፍርድ ቤቶች ፍሬ ነገሩ የተረጋገጠ በመሆኑ የተሰጠው ውሳኔ ባግባቡ በመሆኑ አቤቱታው ተቀባይነት የለውም።ከተያዘው ጭብጥ አንጻርም ቢሆን አመልካች ከበራሃ በጨለማ የ8 ሰዎችን ከብቶች መስረቁ ተረጋግጦ በወ/ሀ/ቁጥር 60(ሐ) መሰረት የተወሰነ ውሳኔ በመሆኑ የሚነቀፍ አይሆንም።ምክንያቱም አመልካች በአንድ ወንጀል ማድረግ ሀሳብ ወይም ቸላተኛነት አንድ የህግ ድንጋጌ በመጣስ ቁጥራቸው ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳይ መድረሱ ከተረጋገጠ አጥፊው ላይ የሚወሰነው ቅጣት የ8 ሰዎችን መብት በጣሱ በ8 ተደራራቢ ወንጀሎች ጥፋታኛ ተብሎ ቅጣት መወሰኑ ህግን መሠረት ያደረገ በመሆኑ የሰር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ አይነቀፍም ተብሎ ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክሯል።

የግራቀኙ ክርክር ከፍ ሲል የተመለከተው ሲሆን ሰበር ችሎቱ ይህንን ክርክር ለመመርመር ከያዘው ጭብጥ ውጪ አመልካች ያቀረባቸው ቅሬታዎችና ክርክሮች

በተመለከተ በጭብጥነት ያልተያዙና የፍሬ ነገር ክርክሮች በመሆናቸው አልተመረመሩም፡፡ የተያዘውን ጭብጥ በተመለተ፣አመልካች ጥፋተኛ ነው ተብሎ ቅጣት የተወሰነበት የተደራረቡ ስምንት ወንጀሎችን ፈጽሟል ተብሎ ነው፡፡አንድ ተከሳሽ ሆነ ብሎ የተደራረቢ ወንጀል ተፈጽሟል የሚባለው ወንጀል አድረጊው ሁለት ወይም ከሁለት በላይ ወንጀሎችን አከታትሎ ከሰራ ወይም በአንድ ድርጊት ሁለት ወይም ከሁለት በላይ ግዙፍ ወንጀሎችን ከሰራ መሆኑ በወ/ሀ/ቁጥር60(1እና2)ላይ ተደንግጓል፡፡ነገር ግን ወንጀል አድራጊው በአንድ የወንጀል ማድረግ ሀሳብ ያደረገው ወንጀል አንድን የህግ ድንጋጌ የሚጥስ ሆኖ ቁጥራቸው ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ አንድ አይነት ጉዳት ያስከተለ ከሆነ በተደራረበ ቅጣት ሊቀጣ እንደሚችል በወ/ሀ/ቁጥር 60(ሐ)ተደንግጓል፡፡

በሌላ በኩል በህግ በተጠበቀ አንድ መብት ላይ የሚደረጉ ከአንድ በላይ የሆኑ የተቀላቀሉ የወንጀል ድርጊቶች በአንድ ወንጀል የማድረግ አሳብ ወይም ቸላተኛነት የተፈጸሙ ሲሆን እና ድርጊቶቹ በሙሉ በአንድ ድንጋጌ ስር የሚሸፈኑ ሲሆን አድራጊው ተመሳሳይ ባህርይ ባላቸው በሁለት ወይም ከሁለት በበለጡ ተደራራቢ የቅጣት ድንጋጌዎች አይቀጣም ተብሎ በወ/ሀ/ቁጥር 61(1)ላይ ተደንግጓል፡፡በህግ በተጠበቀ በዚያው መብት ተደጋግሞ ወይም ተከታትሎ ወንጀል ቢፈጸመም ወንጀሉ የተፈጸመው በአንድ የወንጀል ሀሳብ ወይም ከሆነ አንደ አንድ ነጠላ ወንጀል የሚቆጠር ስለመሆኑ በዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር 2 ላይ ተመልክቷል፡፡ቅጣት ሲወሰን የወንጀል ህጉን ግብና ዓላማ መሠረት ያደረገ ሊሆን ይገባል፡፡የወንጀል ህጉ ጠቅላላ ድንጋጌና የልዩ ክፍሉ ድንጋጌዎች ግምት ውስጥ በማስገባት አመክኖዊ በሆነ መንግድ የህግ ድንጋጌዎችን ይዘት አጣጥሞ በመተርጎም ምክንያታዊና ፍትሀዊ ውሳኔ መወሰን ተገቢ ይሆናል፡፡በመሆኑም በወንጀል ህግ ቁጥር 23 መሠረት ወንጀል ተፈጽሟል ብሎ ድምዳሜ ለመድረስ፣ወንጀልን የሚያቋቁሙ ህጋዊ፣ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ነገሮች ባንድነት ተሟልተው የሚገኙ ስለመሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡በወ/ሀ/ቁጥር 57 እና 58 ጥምር ንባብ መገንዘብ እንደሚቻለው፣አንድ ሰው ለአደረገው ድርጊት ወንጀል ነው ተብሎ ሀላፊ ሊሆን የሚገባው አስቦ አንድን ወንጀል ካለደረገ በቀር በወንጀል ጥፋተኛ ነው ተብሎ ቅጣት ሊወሰንበት አይገባም፡፡

አሁን በተያዘው ጉዳይ፣አመልካች የከባድ ስርቆት ወንጀል የተፈጸመ መሆኑ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ቢሆንም በወ/ሀ/ቁጥር 60(ሐ)መሰረት አመልካች ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች መብት ላይ አስቦ ጉዳት ማድረሱ ጉዳይ ከላይ በተመለከተው መመዘኛና የልማዳዊ

የብዙ ሰዎች ክብቶች በአንድ ላይ ያሉ መሆኑን ያውቃል፡፡አመልካች በኑሮ ልማዱ የሰርቆ ወንጀሉ ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች መብት ላይ ጉዳት ለማድረስ አስቦ ነው ተብሎ በስር ፍርድ ቤት በማሰረጃ አልተረጋገጠም፡፡የአመልካች ድርጊት በማሰረጃ ሳይረጋገጥ ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች መብት ላይ ጉዳት ደርሷል በሚል ምክንያት ብቻ ያለ ገደብ ቅጣት ደምሮ መወሰን፣ በወንጀል ህግ ቁጥር 108 ከተመለከተው የአስራት ቅጣት ጣሪያ፤25 ዓመት በላይ የፅኑ አስራት ቅጣት ለመወሰን የህግ አውጪው አሳብ ነው ለማለት የሚያስችል አለመሆኑን ከፍ ሲል ከተጠቀሱት የህግ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ተችሏል፡፡

በመሆኑም አመልካች ላይ ሊወሰን የሚገባው የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/ህ/ቁጥር 60(ሐ) መሰረት በተደራረቡ 8 ክሶች ወይስ ለአንድ ጥፋት አንድ ቅጣት በሚለውን የወንጀል ህግ ድንጋጌ ቁጥር 31 በመከተል ሊሆን ይገባል የሚለው ነጥብ በአግባቡ ተመርምሯል፡፡በዚህ መሠረት በአመልካች ተፈጸመ የተባለው የወንጀል ድርጊት፣አመልካች ከምሽቱ 4፡00 ሰዓት ሲሆን፣ሌሊት 25 ክብቶችን ሰርቆ በመውሰድ ለመጠቀም ሲል ተይዟል ተብሎ በስርቆት ወንጀል ተከሶ በስምንት ክሶች ጥፋተኛ ነው ተብሎ ተወስኖበታል፡፡የተሰረቁ ክብቶች በአንድ ስብስብ(መንጋ)ሆነው ሲጠበቁ ባሉበት ስለመሰረቃቸው የተረጋገጠ ሲሆን ክብቶቹም የተለያዩ የ8 ሰዎች ሀብቶች ሆነው በመገኘታቸው በመሀበራዊ ፍርድ ቤት እየተረጋገጠ የተመለሱላቸው መሆኑን ከክርክሩ መረዳት ተችሏል፡፡ነገር ግን ከሰርቆት ድርጊት በኋላ ክብቶቹ የአንድ ሰው ሳይሆኑ የብዙ ሰዎች መሆናቸው የተረጋገጠ ቢሆንም አመልካች የሰርቆ ድርጊት በፈጸመ ጊዜ ክብቶቹ የ8 የተለያዩ ሰዎች ክብቶች መሆናቸውን አውቆ በ8 ሰዎች መብት ላይ ጉዳት አድርሷል ለማለት የሚያስችል ፍሬ ነገር በስር ፍርድ ቤት በማሰረጃ አልተረጋገጠም፡፡

አንድ ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ነው ተብሎ ቅጣት ሊወሰንበት የሚችለው፣ድርጊቱን አስቦ መፈጸሙ መረጋገጥ የሚገባው ስለመሆኑ በወ/ህ/ቁጥር 58እና59 ላይ ተደንግጓል፡፡አሁን በቀረበው ጉዳይ አመልካች የፈጸረገው ድርጊት የራሱ ያልሆኑ ክብቶችን ብልጽግና ለማግኘት ሲል መሰረቁ የተረጋገጠ ቢሆንም ክብቶቹ በተሰረቁ ጊዜ በአንድ ስብስብና በአንድ ጥበቃ ስር(መንጋ)የነበሩ ከመሆን አንጻር ሲታይ ከአንድ በላይ ባለሀብቶች ያሏቸው መሆን አለመሆኑን ወንጀል አድራጊው አስቦ የፈጸመው የወንጀል ድርጊት ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች መረጋገጥ ነበረበት፣ነገር ግን ይህ ፍሬ ነገር አልተረጋገጠም፡፡በተለመደው

የከብት አርቢዎች አጠባበቅ ሁኔታዎ ቢሆን ፣ ርቢዎቹ የየራሳቸው ከብቶች ለብቻቸው አሰማርተው ሊያግዱ ወይም ሊጠብቁ የሚችሉ ኒሆን በልዩ ሁኔታ ሁለትና ከሁለት በላይ በመሆንም የየራሳቸውን ከብቶች አውጣጠው ቀላቅላው በጋራ አሰማርተው ሊጠብቁ የሚችሉ ቢሆንም አመልካች 25 ከገቶችን ፣ነረቀው የ8 ሰዎች ከብቶች መሆናቸውን አውቆ ወይም ከአንድ ጊዜ በላይ ቢ፣ቱን ደጋግሞ በመስበር የአደረገው የከባድ ሰርቆት ወንጀል ነው ብሎ ለመደምደም የሚያስችል አይ ፆንም።

የተፈጸመው ድርጊት ሲታይ አንድ የ፣ርቆት ወ ጀል ድርጊት ሲሆን አመልካች የተላለፈው የህግ ድንጋጌም አንድ የህግ ድንጋጌ ነው።የሰረቆ ድርጊቱ ከተፈጸመና አመልካች ከተያዘ በኋላ የተሰረቁ ከብቶች ባለሀብቶች ካአንድ ሰ ነይ (ስምንት ሰዎች) የነው በመገኘታቸው ብቻ አመልካች አሰቦ በ8 ሰዎች መገት ላይ ፡ዳት አድርሷል ብሎ በስምነት ተደራራቢ ክሶች የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔ ፣መወሰን የ፣ንጀል ህጉን ግብና ፡ለማ የተከተለ ውሳኔ ሆኖ አላገኘነውም።አመልካች የሰረቃቸው 25 ከ፣ብቶች በተመለከተ ከ፣ገቶቹ በአንድ መንጋ እያለ የተሰረቁ ሲሆን አመልካች ካብቶቹን በሰረቀ ጊዜ ወይም ለመሰረቅ ሲያስብ አሰቀድሞ ከብቶቹ ከአንድ በላይ ባለሀብቶች ያሏቸው መሆናቸውን ያውቃል ተብሎ ሳይመሰከርበት እያንዳንዱን የከብት ባለሀብት አመላካች ለመጉዳት አሰቦ ድርጊቱን ፈጽሟል ተብሎ ፍሬ ነገሩ ሳይረጋገጥ በሁመ፡ ወረዳ ፍርድ ቤት አመልካች በስምት ክሶች የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔ መወሰኑና ጋህ ውሳኔ በከፍተኛ ፍርድ ቤቱና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሳይታረም መታለፉ የጥ፡ተኛነትና የቅጣት ውሳኔ ከወ/ህ/ቁጥር 61 መሰረት ለአንድ ጥፋት አንድ ቅጣት ተብሎ ፡ተደነገገው ን የህግ ድንጋጌ ባለ፣ጣጤን የተወሰነ ውሳኔ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የ፣ፈጸመበ፣ ነው ብለን በመሆኑ፣ም አመልካች ሊቀጣ የሚገባው ተሸሽሎ በአንድ የወንጀል ድርጊት ብቻ በመሆኑ በቅጣ፡ አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሠረት ተከሳሽ በከበድ ሰርቆ ፡ንጀል የወሰዳቸው 25 ከብቶች ግምታቸው 206 500 ብር በመሆኑና 3 ሆነው ድ፡ጊቱን የ፣ጸሙት በመሆኑ ቅጣት ሊወሰን የሚገባው በደረጃ 7 እርከን 26 ላይ በተመለተው መሠረ፡ ሲሆን ዐ/ህግ በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ማክበጃ የወንጀል ማቋቋሚያ በመሆኑ ማክበጃ ሊያዝ የሚገባው አይደለም ማቅለያን በተመለከተ ዐ/ህግ በተከሳሹ ላይ ሪከርድ ያ፣ቀረበበት በመሆኑ ባወ/ሀ/ቁጥር 82(1)ሀ መሰረት 1 ማቅለያ ችሎቱ በመቀበል ቅጣቱ ከ፣እርከን 25 ላይ ተወ፣ኗል። የዚህ እርከን ፍቅድ ሰልጣን ከ7 ዓመት እስከ 8 ዓመት ጽ ኑ ከ4 ወር እስራት የሚ ይ፣ጠ፡ ሲሆን

የአመልካቹ የግል ሁኔታ ግምት ውስጥ በመግባት በዚህ ጉዳይ የተሰረዉ እስራት ታስቦለት አመልካች በ8(ስምንት) አመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ተወስኗል፡፡

ው ሳ ኔ

1. ተከሳሽ አቶ ማማይ አበራ በቀረበበት ክስ መሠረት የወንጀል ድርጊቱን መፈጸሙ የተረጋገጠው በአንድ የወንጀል ድርጊት፣አንድ የሀግ ድንጋጌ በመተለላፍ በመሆኑ ጥፋተኛ ነው ተብሎ ሊወሰንበት የሚገባው በአንድ ክስ፣የወንጀል ሀጉ ቁጥር 669(3)ለ ብቻ ነው ተብሎ ተሻሽሎ ተወስኗል፡፡
2. የሁመራ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 17546/07ዓ.ም. በቀን 29/11/2007 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ፣ የምዕራባዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 11762 በቀን 05/02/2007ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር/መ/ቁጥር 80720 በቀን 17/05/2008ዓ.ም.የወሰኗቸው ውሳኔዎች በሙሉ ተሻሽለዋል፡፡
3. በአመልካች ላይ ተሸሽሎ የተወሰነው የጥፋተኛነትና የሰምንት ዓመት ጽኑ እስራት የቅጣት ውሳኔን የሁመራ ማረሚያ ቤት እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡ይጻፍ፡፡መዝገቡ ተዘጋ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሩ/ለ